# የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ

ግንቦት 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ

## I. መግቢያ

የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ከእናት ፓርቲው የሚቀዳ የብልጽግና አደረጃጀት ነው፡፡ የብልጽግና ፓርቲም ሴቶች በፓርቲው ውስጥ የራሳቸው አደረጃጀት ኖሮአቸው ለመብትና ጥቅማቸው እንዲታገሉ ፍላጎት እንዳለው በህገደንቡ ላይ በግልጽ አመላክቷል፡፡ የብልጽግና ራዕይ በተሟላ መልኩ ሊሳካ የሚችለውም የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች በንቃት ሲሳተፉና በሂደቱም ተጠቃሚነታቸው ሲረጋገጥ እንደመሆኑ መጠን ለተሳትፏቸው አስተማማኝነትና ቀጣይነት የተደራጀ የጋራ አቅም መስፋፋትና ማደግ ወሳኝነት አለው:: በመሆኑም በሁሉም መስኮች የተጀመረውን የተደራጀ የሴቶች እንቅስቃሴ በማጠናከር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ አቅምን በዘላቂነት ለማሳደግ መረባረብ ስለሚያስፈልግ የቀድሞ የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ አባል ሊጎችና አጋር ሊጎች ለጋራ አላማ በጋራ ለመታገል እንዲያስችላቸው ውህደት ፈጽመው ወጥ የሆነ አገራዊ የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መስርተዋል፡፡

ስለሆነም የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ህብረተሰባዊ ለውጥን የማፋጠን፤ የወቅቱን መድረክ ተልዕኮ ተገንዝቦ በብቃት የመፈፀም፤ ሁሉንም ሴቶች በጋራ አላማ የማሰለፍ፤ የትግል መድረክ ሆኖ የማገልገል፤ እና ጥቅሞችን የማጣጣም ቁልፍ እና ወሳኝ ተልዕኮ ይዞ የተቋቋመ የፖለቲካ አደረጃጀት ነው፡፡ ሊጉ ያነገባቸው አላማዎች የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ብልጽግና በመሆናቸው በተግባር ላይ ከዋሉ ሴቶች ከሚገኙበት ኃላቀርነትና ድህነት አላቆ ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለዲሞክራሲና ለብልፅግና ያበቃቸዋል፡፡ በመሆኑም ብልጽግና ሴቶች ሊግ የሕብረተሰቡ ግማሽ የሆኑትን የኢትዮጵያ ሴቶች ለመለወጥ ቁልፍ መሳሪያ የሆነውን የብልጽግና ፕሮግራሙን በተግባር ላይ ለመዋል በሙሉ አቅሙ ይረባረባል፡፡

መደራጀት ለሴቶች ስንመለከት መብታቸውንና ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር የተሻለ አቅም ይፈጠርላቸዋል፤ በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከተናጠል ይልቅ ተደራጅተው በብቃት በመሳተፍ የላቀ ውጤት ማስመዝገብ ያስችላቸዋል፤ ያሉባቸውን ችግሮች በተናጠል ሳይሆን በጋራ ለመቅረፍና በጋራ ድምፃቸውን ለማሰማት ያግዛቸዋል፡፡ በመሆኑም የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ በኢኮኖሚ፣ በማኀበራዊና በፖለቲካ መስክ ከሚገኙበት

ኋላቀርነትና የበታችነት ተላቀው በሁሉም መስክ እንዲሳተፉ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበር ይታገላል፡፡ እንዲሁም የሴቶችን ሁኔታ ለማሻሻል እንቅፋት የሚሆኑ እንደ ሕግ፣ ባህል ወግና ልማድ ያሉ ጉዳዮች እንዲሁም የነዚህ ነፀብራቅ የሆነው አመለካከት ተወግዶና ተሻሽሎ በውሳኔ ሰጭነት ተግባር እኩል ተካፋይ እንዲሆኑ ይሠራል፡፡ ሊጉ በተለይም ሕብረተሰቡ በሴቶች ላይ እንዲሁም ሴቶች በራሳቸው ላይ ያላቸው የዝቅተኛና የበታችነት አመለካከት ተወግዶ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ጤናማ ግንዛቤ መፍጠር፣ ሁኔታዎችንም ማመቻቸትና ማዳበር ላይ በማተኮር ይሰራል፡፡

ሊጉ የብልጽግና ፕሮግራሙን በስራ ላይ ለመዋል በሚያስችል ደረጃ መላ ሴቶችን የማንቀሳቀስ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት የሚችለው ከላይ እስከ ታች የሀሳብና የተግባር አንድነት ሲኖረው ነው፡፡ በሊጉ መዋቅር በየደረጃው ይህንን የተግባር እና የሀሳብ አንድነት በመፍጠር እና በቀጣይነት ለማጎለበት እንዲቻል በአደረጃጀት ውስጥ ጠንካራ አስተማማኝ እና ቀጣይነት ያለው ዲሞክራሲያዊ መድረክ ያስፈልገዋል፡፡ መተዳደሪያ ደንቡ በሴቶች ሊግ ውስጥ የሀሳብ ትግል በነፃነት መንፈስ የሚካሄድበትን ዲሞክራሲያዊ መድረክ ሕጋዊ እና ተቋማዊ መልክ በማስያዝ አስተማማኝ ያደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ መተዳዳሪያ ደንባችን በሊጉ የአመራር አካላትና አባላት መካከል ጠንካራ የሀሳብና የተግባር አንድነት፣ በግለሰባዊ ትስስር ምትክ በተቋማዊ አሰራር ላይ የተመሰረተ የአሰራርና የአመራር ስርዓት እንዲኖረን በማድረግ የብልጽግና አላማዎቻችን በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችለናል፡፡ ስለሆነም የ4ኛው የሊጉ ጉባኤ ባአስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የብልፅግና ፓርቲ ውህደትን ተከትለን የአጋር ፓርቲ ሊጎች እና ሁሉም ክልል ያሉ የብልፅግና ፓርቲ ሊጎች ጋር ተወያይተን በተስማማነው መሠረት በጋራ ይህን መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅተናል፡፡

# <u>ምዕራፍ አንድ</u>

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## አንቀፅ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ «የብልጽግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ መተዳዳሪያ ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 2

## ስያሜ

የሊጉ መጠሪያ «የብልፅግና - ርቲ የሴቶች ሊግ» ወይም «የብልጽግና ሴቶች ሊግ» ተብሎ ይጠራል፡፡

## አንቀፅ 3

## አርማ

ሊጉ ስራውን ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚያስችለው የራሱ አርማ ይኖረዋል፡፡

## አንቀፅ 4

## የአርማ ትርጉም

አርማው በሃገራችን ያሉ ሴቶች በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ በሰላም እና በልማት ዙሪያ ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያጠናክር እና የሴቶችን አንድነት የሚያጎለብት እንዲሁም የሴቶችን ሁለንተናዊ ብልጽግናንና የሴቶችን እኩልነት የሚያረጋግጥ መልዕክት ይኖረዋል፡፡

## አንቀፅ 5

## የሊጉ የስራ ቋንቋዎች

1. ሊጉ ለሁሉም የአገራችን ቋንቋዎች ሙሉ እውቅና ይሰጣል፤
2. የሊጉ የስራ ቋንቋ የሀገሪቱ ህገ መንግስት እና ክልሎች በህገ መንግስታቸው የስራ ቋንቋ ይሆናሉ ብለው ያጸደቋቸው ቋንቋዎች ይሆናሉ፡፡
3. የሊጉ የየደረጃው ፅ/ቤቶች የየራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ቢያንስ አንድ የሊጉን የስራ ቋንቋ  በተጨማሪነት መጠቀም ይችላሉ፡፡

## አንቀፅ 6

## የሊጉ ልሳን

የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የሊጉን አቋሞችና እንቅስቃሴዎች ይፉ የሚያደርግበት የእራሱ ልሳን ይኖረዋል፡፡ የሊጉ ልሳን መጠሪያ የሴቶች ሊግ ልሳን ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 7

## የሊጉ ጽሕፈት ቤት

1. የሴቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አዲስ አበባ ከተማ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጸበቀ ሆኖ ሊጉ በክልል፤ በከተማ አስተዳደር፤ በዞን፤ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ፣ በክፍለ ከተማ እና በቀበሌ ፅ/ቤቶች ይኖሩታል፡፡

## አንቀፅ 8

## የብልጽግና ሴቶች ሊግ ዓላማዎች፣ መርሆች እና እሴቶች

### 1. የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አላማዎች

የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.1 የብልጽግና ፓርቲ ፕሮግራም በህዝቡ ውስጥ ሰርፆና ተግባራዊ ሆኖ መላው የአገራችን ሴቶች ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፤

1.2 ሴቶች በዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ በየደረጃው የልማት የዴሞክራሲና የሰላም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፤

1.3 ሴቶች ህገ-መንግስቱ ያጎናፀፋቸውን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በትክክል ስራ ላይ እንዲውሉ ጠንካራ አደረጃጀት በመፍጠር ለመብታቸው እንዲታገሉ ማስቻል፤

1.4 የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የሴቶችን አቅም በመገንባትና የሴቶች እኩልነት የሚገድቡ ባህላዊና ልማዳዊ ተጽዕኖዎችን በመለየት ለሀገር ዕድገት እና በሴቶች ላይ የሚፈጠሩትን ተጽዕኖ በማስገንዘብ እንዲወገድ በማድረግ ሴቶች በውሳኔ ሰጪነት እኩል እንዲሳተፉ ማድረግ፤

1.5ሴቶች የፈጠራ ዝንባሌያቸው እንዲጎለብት፣ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና የስራ ባህላቸው ዳብሮ ስራ ፈጣሪ በመሆን እራሳቸውን እና ሀገራቸውን ከድህነት ለማውጣት የሚታገሉ እንዲሆኑ ማድረግ፤

1.6ሴቶች ህብረ ብሄራዊ አንድነታቸውን በመጠበቅ የመተሳሰብና የመረዳዳት ባህል በማጎልበት በሀገራዊ ጉዳዬች ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፡፡

## 2. የብልጽግና ሴቶች ሊግ መርሆዎች

የብልጽግና ሴቶች ሊግ መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ) ህዝባዊነት፤

ለ) ዴሞክራሲያዊነት፤

ሐ) የህግ የበላይነት፤

መ) ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት፤

ሠ) ተግባራዊ እውነታ፤

ረ) ሀገራዊ አንድነትና ህብረ-ብሄራዊነት፤

## 3. የብልጽግና - ርቲ ሴቶች ሊግ እሴቶች

የብልጽግና - ርቲ ሴቶች ሊግ የሚከተሉት እሴቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ. እህትማማችነት

ለ. መከባበርና መቻቻል

ሐ. ህብረብሔራዊ አንድነት

መ. የዜጎች ክብርና የስርዓተ ጾታ እኩልነት

ሠ. ነጻነት

ረ. እኩል ተሳትፎና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት

## አንቀጽ 9

## የብልጽግና ሴቶች ሊግ የአሠራር ስርአት

### 1.የብልፅግና ሴቶች ሊግ የአሰራር መርሆዎች

1.1 የብልጽግና ሴቶች ሊግ የአገሪቱን እና የክልሎችን ሕገ መንግስትን እና ሌሎች ሕጎችን በማክበር ተግባራቱን ያከናውናል፤

1.2 በሴቶች ዙሪያ የወጡ ዓለም አቀፍ ስምምነቶእ እና ህጎች እነዚህን ሀገራችን ወስዳ ተግባራ እያደረገቻቸው ያሉ ህጎች፣ ደንቦች የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ የወጡ ፖሊሲዎች ፓኬጆች፣መመሪያዎች እና ደንቦችን በግንባር ቀደምትነት ተፈጻሚ እንዲሆኑ የጋራ ርብርብ ያደርጋል፤

1.3 የሊጉ አባላት በተግባራቸው ግንባር ቀደም በመሆን እርስ በርስ በመማር በመከባባር እና ሴቶች ወደ ፊት እንዲወጡ የማስችል ስርዓት ይፈጥራል፤

1.4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የሊጉ አባላት የመፈጸም፣ የማክበርና የማስከበር ሃላፊነት አለባቸው፤

1.5 አባላት የግል ሃሳባቸውን የማራመድ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሊጉን ውሳኔ የመፈጸምና የማስፈጸም ሃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፤

1.6 ማንኛዋም አባል በሊጉ ውስጥ እኩል ድምጽና በውሳኔ ሂደቶች ውስጥ አንድ ድምጽ ብቻ ይኖራታል፤

1.7 በብልጽግና ሴቶች ሊግ አሰራር ውሰጥ የአባላትን የሀሳብና የተግባር አንድነት በሚፈጥር ዲሞክራሲዊነትን በተከተለ ዲስኘሊንን የስራ ቅልጥፍናንና ውጤታማነትን በሚያጠናክር የግልና የጋራ ኃላፊነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል መርሆ ላይ የተመሰረተ ነው።

1.8 በብልጽግና ሴቶች ሊግ አሰራር የአላማ ጽናትና የስራ ተነሳሽነት እንደበለጽግ የአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በሚያስፍን መልኩ ይሆናል።

1.9 የብልጽግና ሴቶች ሊግ ድክመቶችን በአግባቡ እየገመገመ ስህተቶቹን የማረም ጥንካሬዎቹን የማጎልበት ገንቢ የመተራረም ስርዓት እንዲጠናከር የሚያደርግ መርሆ ይከተላል።

## 2. የብልጽግና ሴቶች ሊግ የውሳኔ አሰጣጥ አግባብ

2.1 በየደረጃው የሚገኙ የብልፅግና ሴቶች ሊግ አካላት ማንኛውንም ውሳኔ የሚያሳልፉት በጉዳዩ ላይ በበቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ በቂ ክርክርና ውይይት መደረጉን ካረጋገጡ በኋላ በድምጽ ብልጫ ይሆናል።

2.2 አንድ ሰው አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል። ለውሳኔ የቀረበ ሀሳብ የጋር መመሪያ ሆኖ ሊያገልግል የሚችለው ከተገኘው ምልዐተ ጉባኤ 50%+1 ይሆናል። ተሰብሳቢው በእኩል ድምፅ ከተከፈለ ሰብሳቢዋ ያለችበት ወገን ድምፅ አሸናፊ ይሆናል።

2.3 በየትኛውም አካል ስብሰባ ላይ ምልዓተ-ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው ከጠቅላላ የስብሰባው ተካፋዮች 50%+1 ሲገኙ ነው::

2.4 ምልአተ ጉባኤ 50%+1 ሲሆን በስብሰባ ላይ በሞት፣ በቅጣት፣ በሰንብት ወይም በክህደት በቀጣይነት የማይገኙት ምልአተ ጉባኤ ላይ ታሳቢ አይደረጉም::

2.5 ሆን ብሎ ምልአተ ጉባኤን ማጓደል በዲስኘሊን ያስጠይቃል::

2.6 50%+1 ድምፅ ያገኘ የውሳኔ ሀሳብ በወሰነው አካልና ከሱ በታች ባሉ አካላትና አባላት በሙሉ ተፈፃሚ ይሆናል::

2.7 በማንኛውም የኮሚቴ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው ለኮሚቴው አባላት በተናጥል ወይም ደግሞ ከኮሚቴው በታች ላሉ አካላት በሚሰጥ የጋራ ወይም የተናጠል ሀላፊነት ይሆናል::

2.8 ማንኛውም የበታች ኮሚቴ ወይም የበታች ኮሚቴዎች አባል ከበላይ አካል የመጣለትን ውሳኔ የመፈፀም ግዴታ አለበት::

2.9 በኮሚቴ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ወይም ያልተስማማ አባል ውሳኔዎቹን እየፈፀመ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ህጋዊ በሆነ መንገድ የመጠየቅ መብት አለው::

2.10 በማናቸውም የውሳኔ ሀሳብ ላይ ከተሰብሳቢው አባል 1/3ኛ በሚያህሉት እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ከቀረበ እንደገና የመታየት ጥያቄው ለውይይት ክፍት ይሆናል:: 50%+1 ከሆነ እንደገና መታየት አለበት ብለው ከወሰኑ ጉዳዩ እንደ አዲስ ታይቶ ይወሰናል::

2.11 በአንድ መድረክ በተወሰነ ውሳኔ ላይ አቤቱታ ቀርቦ በዚያው መድረክ ተቀባይነት ካገኘ ተደጋጋሚ አቤቱታዎች አይቀርቡም:: በጉዳዩ ላይ አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው ውሳኔውን በተግባር እየፈፀሙ በሂደት በሚከፈት የስብሰባ አጋጣሚ ወይም የፅሁፍ ፊርማ በማሰባሰብ ብቻ ይሆናል::

2.12 እንደገና ይታይልን በሚል ጥያቄ የወሰነው አካል በስብሰባ ላይ ባለበት በቃል ወይም በፅሁፍ፣ ወሳኙ አቤቱታ ቀርቦ ጉዳዩ ከላይ በቀረበው መሰረት ይታያል:: ወሳኙ አካል ከተበተነ ደግሞ በፅሁፍ አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል:: በፅሁፍ የሚቀርብ አቤቱታ አቅራቢዋ ግለሰብ አቤቱታዋን በፅሁፍ አዘጋጅታ ለሰብሳቢዋ ታስረክባለች:: ሰብሳበዊ አቤቱታውን ወደ ሚመለከታቸው አባላት ሁሉ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በማሰራጨት አቤቱታውን በሚደግፉ ሁሉ እንዲፈርሙ ታደርጋለች:: ከሚመለከታቸው አባላት ውስጥ 1/3ኛው ከፈረሙ ጉዳዩ በሚቀጥለው መደበኛ ስብሰባ ወይም ደግሞ እንደአመችነቱ ቀደም ብሎ በሚጠራ አስቸኳይ ስብሰባ ላይ እንዲታይ ይደረጋል::

2.13 መደበኛ ስብሰባዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሄድ ይኖርባቸዋል የሚቀርቡ አጀንዳዎች አስቀድመው ተሰብባቢዎችን እንዲያውቋቸው መደረግ አለበት፡፡

2.14 የሚካሄደው ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ ተይዞ ውሳኔዎች ተጽፈው ሊፀድቁና በሰነድነት ሊያዙ ይገባል፡፡ ውሳኔውን የሰጠት አባላትም በፊርማቸው ማረጋገጥና የአባላት ብዛት ለፊርማ የማያመች ቁጥር ከሆነ በኘሬዝዲየሙ አባላት መፈረም አለበት

2.15 የብልፅግና ሴቶች ሊግ አሰራሮች በግልፅነትና በተጠያቂነት መርህ ላይ የተመሰረቱ ይሆናሉ፡፡

2.15.1 የበላይ አካላት ውስኔዎች በተለየ ሁኔታ በምስጢር ተጠብቀው እንዲቆዩ ካልተወሰነ በስተቀር በተዋረድ ለአባላት ይገለፃሉ፡፡

2.15.2 በተለየ ሁኔታ በምስጢርነት ተጠብቀው ሊቆዩ የሚችሉ ጉዳዮች በሊጉና በ- ርቲው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

2.15.3 በየደረጃው የሚገኙ የብልፅግና ሴቶች ሊግ የአመራር አካላት የስራ እንቅስቃሴያቸውን የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርት በተመደበላቸው ወቅት ለበላይ አካላት ያቀርባሉ፡፡

2.15.4 በየደረጃው የሚገኙ አካላት በወሰኗቸው ውሳኔዎች ሁሉ ሀላፊነት ይወስዳሉ፡፡ በተጨማሪም ሀላፊነትን ባለመወጣት ወይም ከተሰጠ ሀላፊነት ውጭ ከተሰማሩ ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፡፡

2.15.5 ተጠያቂነቱ እንደ ሁኔታው በሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ወይም በሀገሪቱ ህጎች መሰረት ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ ርምጃወችን ያስወስዳል፡፡

## 3. የብልጽግና ሴቶች ሊግ የምርጫ አፈጻጸም ስርዓት

3.1 ማንኛዋም አባል ለምርጫ እጩ/ተወዳዳሪ/ ማቅረብ ትችላለች፡፡

3.2 ሁሉም መራጮች እኩል ድምጽ አላቸው፡፡

3.3 ማንኛዋም አባል ለውድድር የቀረበች ዕጩ ተመራጭን በሚመለከት ማብራሪያ እንዲሰጣት የመጠየቅ፣ ደግፎ የመከራከር ወይም እንዳትወዳደርም ሆነ እንዳትመረጥ መቃወም ትችላለች፡፡

3.4 ምርጫዎች የሚካሄዱትን ነጻና ቀጥተኛ በሆነ አግባብ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በሚስጥር ወይም በግልጽ ይከናወናል፡፡

3.5 ማንኛዋም ለውድድር የተጠቆመች ሴት ዕጩ ሆና ልትመዘገብ የምትችለው ከተሰብሳቢው 1/3ኛ ድምጽ ድጋፍ ስታገኝ ነው፡፡

3.6 ተወዳዳሪዋ ለታጨችበት ቦታ ልትመረጥ የምትችለው ከተወዳዳሪዎቹ አብላጫ ድምጽ ስታገኝ ነው፡፡

3.7 ማንኛው አባል ስለ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የምታቀርበው ድጋፍም ሆነ ተቃውሞ በሀቅ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ የተዛባ መረጃ በመስጠት የተዛባ ድምዳሜ ላይ ለማድረስ መሞከር የተከለከለ እና በኃላፊነትም የሚያስጠይቅ ነው፡፡

## 4. የብልጽግና ሴቶች ሊግ የዲስፒልን ግምገማ ሂስና ግለሂስ ስርዓት

4.1 ማንኛውም አባልም ሆነች አመራር አካል የሊጉን ኘሮግራም ደንብ መመሪያዎች ዕቅዶችና ውሳኔዎች የምታከብር እና በግንባር ቀደም በመፈፀም እና በማስፈፀም ራሷን ከማንኛውም ቡድንተኝነት እና አዱላዊ አሰራር ነፃ የሆነች፣ ከሀሜት እና አሉባልታ እርስ በርስ ከመጠቃቃት ነጻ የሆነች በሞክራሲያዊ ሂደት የምታምን ልትሆን ይገባል፡፡

4.2 መላ የሊጉን አባላት በእምነትና በፍላጎት ላይ የተመሰረትና ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ዲስፒሊን አክባሪነትንና አስከሪነትን በተግባር የመተርጎም አሰራር ይከተላል፡፡

4.3 ግምገማ ከአዎንታዊ ሆነ አሉታዊ ተሞክሮዎቹ ገንቢ ትምህርት የሚገበይበት ሂስና ግለሂስ በአባላት ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች ለማስተካከል ሲባል የሚካሄድ የሊጉ ቋሚ አሰራሮች ናቸው፡፡

4.4 የሚካሄዱ ግምገማዎች በተጨባጭ መረጃዎች ላይ የተመሰረቱ ግለሰቦችን ሳይሆን ስራን ማዕከል ያደረጉ ሂስና ግለሂሶችም በዲሞክራሲያዊ በአግባብና ገንቢ በሆነ መንገድ የሚከናወኑ ይሆናሉ፡፡

4.5 አባላት በተሳሳቱባቸው ጉዳዮች ላይ ቅንና አስተማሪ የሆኑ ግስሂሶችን በይፋ መወስድ በሌሎች ስህተቶች ላይም ገንቢ ሂስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከሁሉ በላይ ስህተቶችን አስቀድሞ ማስቀረት የሚያስችሉ የድጋፍና ክትትል ስርአቶችን ዘርግቶ በስራ ላይ ማዋል፡፡

## 5. የብልጽግና ሴቶች ሊግ የቅጣት አፈጻጸም

5.1 ቅጣት የሊጉን ብቃትና ጥራት የማረጋገጥና ማጠናከር የአባላትን ፖለቲካዊ ግንባታን ዲስኘሊን የማጎልበት አስታማሪና ገንቢ ዓላማ ይኖረዋል፡፡

5.2 ዲስኘሊን ጉድለት እንደ ጥፋቱ እየተመዘነ የዲስኘሊን ቅጣት ይሰጣል፡፡

5.3 የቅጣት አይነቶች

ሀ. ማስጠንቀቂያ

ለ. ከሊጉ ኃላፊነት ለተወሰነ ጊዜ ማገድ

ሐ. ከከሊጉ ኃላፊነት ዝቅ ማድረግ

መ. ከሊጉ ኃላፊነት ማውረድ

ሠ. ከሊጉ አባልነት ለተወሰነ ጊዜ ማገድ

ረ. ከሊጉ አባልነት ማባረር

5.4 እንደ ጥፋቱ ሁኔታ አንድ ወይም የተለያዩ ቅጣቶችን በአንድ ጊዜ ተፈጻሚ ማድረግ ይቻላል፡፡

5.5 ከሊጉ አባልነት የሚያስወግዱ ጥፋቶች

ሀ. ከሊጉ የተለየ ኘሮግራምና ስትራቴጂ ይዞ ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀስ፡፡

ለ. የብዙሀን ውሳኔን ሆነ ብሎ ተግባራዊ አለማድረግና ማደናቀፍ፡፡

ሐ. የከፋ የሰነ-ምግባር ጉድለት

መ. በሊግ ውሰጥ ቡድን መፍጠር

ሠ. የድርጅት መርሆዎችን በተደጋጋሚ መጣስ

ረ. በወንጀል ተከሶ በፍ/ቤት የተፈረደበት

6.6. ነማንኛዋም አባል የሚቀርብበትን ክስ የማወቅ፣ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ የመከራከሪያ አለኝ የምትለውን መረጃ የማቅረብ መብት አላት፡፡

6.7 ቅጣት የተወሰነባት አባል ቅሬታዋን ለሚመለከተው አካል የማቅረብ መልስ የማግኘት መብት አላት፡፡

6.8 ስለ ቅጣት አፈጻጸም ተጨማሪ መመሪያ በሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሊወጣ ይችላል፡፡

# ምዕራፍ 2

## አባልነት

## የአባልነት መብትና ግዴታ

## አንቀፅ 10

### የብልፅግና ሴቶች ሊግ አባል ስለመሆን

1. የብልፅግና ሴቶች ሊግ አባል ለመሆን ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች የምታሟላ ማንኛዋም ኢትዮጵያዊት ዜጋ የሊጉ አባል መሆን ትችላለች።
   - 1.1. የብልፅግና ፓርቲ አላማዎችና የሴቶች ሊግ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለች እና ለተግባራዊነቱ በፅናት የምትታገል፤
   - 1.2. በሊጉ ህጎችና መመርያዎች መሰረት በተለያዩ የሊጉ መዋቅሮችና ስራዎች ውስጥ በመሳተፍ ተጨባጭ አስተዋፅኦ ለማድረግ ዝግጁ የሆነች፤
   - 1.3. በሴቶች ዙሪያ የወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችን የሚታከብር ለመፈጸምና ለማስፈጸም ዝግጁ የሆነች፤
   - 1.4. መልካም ስነ ምግባር ያላትና በህብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያላት፤
   - 1.5. በህብረ ብሄራዊነት እና በሀገራዊ አንድነት ላይ ፅኑ አቋም ያላትና ዋልታ ረገጥ አመለካከትና ተግባሮችን በፅናት የምትታገል፤
   - 1.6. ዜጎችንና ህዝቦችን በእኩልነት የምታገለግል፣ በስርዓተ ፆታ እኩልነት የሚታምን፣ የህዝብ ጥቅምን የምታስቀድም፣ ከሙስናና ብልሹ አስራርሮች ራሷን ያራቀች እና ሌሎችንም የምትታገል፤
   - 1.7. የሊጉን የአባልነት መዋጮ ለመክፈል ዝግጁ የሆነች፤
   - 1.8. እድሜዋ አስራ ስምንት አመት እና ከዚያ በላይ የሆነች፤
   - 1.9. የብልፅግና ፓርቲ አባል የሆነች፤

## አንቀፅ 11

## የአባላት መብቶች

1. ሁሉም የብልፅግና ሴቶች ሊግ አባላት እኩል መብት አላቸው
2. በሊጉ አካላት ምርጫወች የመምረጥ እና የመመረጥ

3. በሊጉ ጉባኤዎች የመሳተፍ፤ በውይይት የመካፈል በድምፅ በሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ ድምፅ የመስጠት፤ በማንኛውም ጉዳይ ላይ በህጋዊ መድረኮች ሀሳቡን በፅሁፍም ሆነ በቃል የማቅረብ
4. ስለራሷ፤ ስለአካሏ ስለፓርቲው ማወቅ የሚገባትን ነገር አስከ ሊጉ ማአከላዊ ኮሚቴ የመጠየቅና መልስ የማግኘት
5. ማንኛዋም አባል ያለበቂ ምክንያትና ያለ ህጋዊ አካል ውሳኔ ቅጣት አይወሰንባትም። በህጋዊ መንገድ ከተወሰነባትም በዝርዝር እንድታውቀው ይደረጋል ከግል ማህማሯ ጋርም ተያይዞ ይቀመጣል።
6. ማንኛዋም አባል በሊጉ ውስጥ በእኩል ትስተናገዳለች።
7. ማንኛዋም የሊጉ አባል በየትኛውም ጊዜ ከአባልነት ለመልቀቅ ከፈለገች በጽሁፍ አመልክታ እና በእጇ የሚገኙ የፓርቲው ንብረቶች ሀላፊነት በተሞላበት መንገድ አስረክባ መልቀቅ ትችላለች

## አንቀፅ 12

## የአባላት ግዴታዎች

1. የሴቶች ሊግ ፕሮግራም፣ መተዳደርያ ደንብ፣ መመርያዎች ውሳኔዎችና እቅዶችን የማክበር፣ የመገዛት እና ለተግባራዊነታቸው በግንባር ቀደምትነት የመታገል።
2. በሴቶች ዙሪያ የወጡ ህገመንግስታዎ መብቶችን፤ፖሊስዎችን ፣ፓኬጆችን በግንባር ቀደም የመፈፀም የማስፈፀም ሚና የሚትጫወት፤
3. የሴቶች ሊግ ደህንነትና ምስጢር የመጠበቅ፤
3. የሴቶች ሊግ መዋጮ የማዋጣት ግዴታ አለባት፤
4. በምትገኝበት የስራ መስክና ሀላፊነት የሊጉን አንድነት፤ ጥራትና፤ ጥንካሬ፤ የ- ርቲውን የፖለቲካ እሳቤዎች ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ሙሉ ተሳትፎ የማድረግ

## አንቀፅ 13

## አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

1. የብልፅግና ሴቶች ሊግና የብልጽግና - ርቲ ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን የማታከብርና ተግባራዊ የማታደርግ ከሆነ፤
2. የብልፅግና ሴቶች ሊግ ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥል ተጨባጭ ስራ የሰራች ከሆነ፤
3. በገዛ ፈቃድዋ ለመልቀቅ አመልክታ ውሳኔ ሲሰጥበት

# ምዕራፍ ሶስት

## የብልፅግና የሴቶች ሊግ መዋቅር

## አንቀፅ 14

1. የብልፅግና ሴቶች ሊግ አወቃቀር ና የአመራር አካላት የብልፅግና - ርቲ ድርጅታዊ አወቃቀርን ተከትሎ የሚሄድ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት

   1.1 ፌደራል

   1.2 ክልል

   1.3 ዞን/ከተማ አስተዳደር

   1.4 ወረዳ/ልዩ ወረዳ/ከተማ አስተዳደር/ክፍለ ከተማ

   1.5 ቀበሌ ናቸው::

2. ሊጉ የሚከተሉት ተቋማዊ መዋቅሮች ይኖሩታል ::

   3.1 ጉባኤ

   3.2 ማዕከላዊ ኮሚቴ

   3.3 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

   3.4 ፕሬዘዳንት

   3.5 ም/ፕሬዘዳንቶች

   3.6 የቁጥጥር ኢንስፔክሽን ኮሚሽን

   3.7 የሊጉ ዋና ጽ/ቤት

   3.8 የሊጉ የክልል ፅህፈት ቤቶች

   3.9 የሊጉ የዞን፤ የከተማ፤ የክፍለ ከተማ፤ የወረዳ እና የቀበሌ ፅህፈት ቤቶች

4. የሊጉ መሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳት ፤ አባላት በሚገኙባቸው ቦታወች ይቋቋማሉ::

## አንቀፅ 15

## የሊጉ ጉባኤ ፤ የክልል፣ የዞን፣ የከተማ አስተዳደርና፣ የክፍለ ከተማ፣ የወረዳ ና የቀበሌ የኮንፈረሶች አወቃቀር

1. የሊጉ ጉባኤ በፌዴራል ደረጃ ይቋቋማል፡፡
2. በክልል ደረጃ ክልላዊ ኮንፈረንስ የሚኖር ሆኖ በየደረጃው በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር፣ በክፍለ ከተማና ቀበሌ ኮንፈረሶች ይካሄዳሉ፡፡

3. የኮንፈረንስ ውክልና በዋናነት የሴቶችና አባላትን ብዛት መሰረት ያደረገ ሆኖ አነስተኛ የህዝብ ብዛት ቁጥር ያላቸውን የብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች አባላት ውክልና ባረጋገጠ መልኩ ይዋቀራል፡፡
4. በመደበኛ ጉባኤና በእያንዳዱ ኮንፈረንስ ወቅት ከሚመረጡ ጉባኤተኞች እና የኮንፈረስ ተሳታፊዎች ብቃት ያላቸውን አዳዲስ አባላት ያካተተ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 16

## የሊጉ የጉባኤ

1. ጉባኤው የሴት ሊግ የበላይ አመራር አካል ነው ፡፡
2. የብልፅግና ሴቶች ሊግ ጉባኤ ከሁለት ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ተከል ይካሄዳል፡፡ ሆኖም አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም ማዕከላዊ ኮሚቴው እስከ ስድስት ወር ሊያራዝም ይችላል፡፡
3. ጉባኤው በፕሬዝዳንቷ እና በምክትል ፕሬዝዳንቶች ሰብሳቢነት ይመራል፡፡
4. የጉባኤው ተሳታፊዎች ቁጥር ከ500 በላይ ሆኖ፤ ልዩ ድጋፍ የሚሹና አነስተኛ የህዝብ ቁጥር ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያደርግ መልኩ ስብጥሩ ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፤
5. የሊጉ ጉባዔ አባላት ውክልናና ተሳትፎ በአባላት ቁጥር መሰረት ያደረገ ሆኖ፤ ዝርዝሩ ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፤
6. የብልፅግና ሴቶች ሊግ ማአከላዊ ኮሚቴ አባላት ቢያንስ በ1/3ኛ በድምፅ ብልጫ ሲወሰን አስቸኳይ ስብስባ ሊጠራ ይችላል፡፡
7. የብልፅግና ሴቶች ሊግ ቁጥጥር ኮሚሽን የቋሚ ጉባኤ አባላትን 1/3 ኛ የድጋፍ ድምፅ ካገኘ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ለማድረግ ይችላል፡፡
8. አስቸኳይ ጉባኤ በሚጠራበት ጊዜ አስቀድሞ በተካሄደው መደበኛ ጉባኤ የተካፈሉት ጉባኤተኞች በቀጥታ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡
9. የአስቸኳይ ጉባኤ ምልዐተ ጉባኤ 50+1 ነው፡፡
10. የሊጉ ማአከላዊ ኮሚቴ እና የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን አባላት በቀጥታ በጉባኤው ይሳተፋሉ፡፡
11. ለመደበኛ ጉባኤ እና አሰቸኳይ ጉባኤ የጉባኤዎቹ ጊዜ፤ ቦታና አጀንዳዎችን አሰቀድሞ በሊጉ ዋና ጽ/ቤት በኩል መገለፅ ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ 17

## የሊጉ የጉባኤ ተግባርና ሀላፊነት

1. የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል እንደ አስፈላጊነቱ ይቀይራል፡፡
2. የሴቶች ሊግ የሚመራበትን የስራ አቅጣጫ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጣል፤ የስራ ዕቅድ ያጸድቃል፡፡
3. የብልፅግና ሴት ሊግ ማእከላዊ ኮሚቴና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የቁጥጥር ኢንስፔክሽን ኮሚሽን አባላትን በሚስጥር ድምጽ ይመርጣል፡፡
4. የብልፅግና ሴት ሊግ ማእከላዊ ኮሚቴ የቁጥጥር ኮሚሽን ሪፓርቶች ያደምጣል፣ ይገመግማል፣ ያፀድቃል፡፡
5. ሊጉ ለሌሎች አጋር ሊጎች ጋር ወህደት ወይም ቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር የወሳኔ ሀሰብ ያፀድቃል፡፡
6. የማዕከላዊ ኮሚቴ እና የቁጥጥር ኢንስፔክሽን ኮሚሽን አባላት ዕገዳ እና ስንብት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
7. የሊጉን ሰምና ዓርማ ያፀድቃል፤ ያሻሽላል፤ ይለውጣል፡፡
8. የብልፅግና ሴቶች ሊግ ፕሬእዳንት እና ምክትል ፕሬዘዳንቶችን በምስጥር ድምጽ በቀጥታ ይመርጣል፡፡
9. ጉባኤው መደበኛ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው አማካይነት ጉባኤውን በተመለከተ ሪፓርት ቀርቦ እንዲፀድቀ ይደረጋል፡፡
10. በጉባኤው ላይ ለውይይት የሚቀርቡት አጀንደዎች አስቀድመው በጉባኤተኛው እንዲፀድቁ ይደረጋል፡፡
11. በጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔ በጉባኤው በተመረጡ የውሳኔ አርቃቂ አካል ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ድምፅ በመስጠት ይከናወናል፡፡ የጉባኤ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፉሉ፡፡
12. ጉባኤው ከተግባርና ሀላፊነቱን በሙሉ ውይም በከፊል ለማአከላዊ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 18

## የሴቶች ሊግ ማዕከላዊ ኮሚቴ

1. ማአከላዊ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለጉባኤው ሆኖ
2. ከጉባኤው ቀጥሎ ያለ የሴቶች ሊግ ከፍተኛ አመራር አካል ነው፡፡

3. ማዕከላዊ ኮሚቴው በቀጥታ በነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ከጉባኤው አባላት በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ በሚመረጡ አባላት የሚመሰረት ነው፡፡

4. የማአከዊ ኮሚቴው አባላት ብዛትና ስብጥር በአባላት ቁጥር መሰረት እና አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ክልሎች ተሳትፎ ያረጋገጠ ሆኖ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ በማአከላዊ ኮሚቴ ይወጣል፡፡

5. ማዕከላዊ ኮሚቴው በየስድስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም የስራ አስፈጻሚው ካመነበት ወይም ከማአከላዊ ኮሚቴው አባላት መካከል አንድ ሶስተኛ ሲጠይቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ አስቸኳይ ሰብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

5. የማአከላዊ ኮሚቴ ምላዕተ ጉባኤ ከአባላት ከ50%+1 የተገኙበት ይሆናል፡፡

6. የማዕከላዊ ኮሚቴ መድረክ በፕሬዘዳንቷ እና በምክትል ፕሬዘዳንቷ በጋራ ይመራል፡፡

7. **የማአከላዊ ኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነት የሚከተሉት ናቸው፡፡**

7.1 ከአንድ ጉባኤ እስከ ሚቀጥለው ጉባኤ ሊጉን በበላይነት ይመራል፡፡

7.2 የማዕከላዊ ኮሚቴው በፕሬዘዳንቷ ይመራል፡፡

7.3 ማዕከላዊ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባውን በስድስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል ፡፡

7.4 የጉባኤውን ውሳኔዎች መሠረት በማድረግ ዕቅዶች ይነድፋል፡፡

7.5 የሊጉን ፕሮግራም መተዳደሪያ ደንብ የጉባኤ ውሣኔዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

7.6 በብልፅግና ሴቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ ላይ አከራካሪ ነጥቦች ሲኖሩ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

7.7 መተዳደሪያ ደንቡን ለማስፈፀም የሚያስችሉ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ያፀድቃል፡፡

7.8 ለሴቶች ሊግ ሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ የሆኑ መዋቅሮችን፣ ያደረጃል፣ ያሻሽላል፡፡

7.9 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ሪፓርት ያደምጣል፣ ይገመግማል ውሳኔ በሚሹ ነጥቦች ላይ ይወስናል፡፡

7.10 የብልጽግና ሴቶች ሊግ የስራ አስፈፃሚን ይሰይማል፡፡

7.11 በማአከላዊ ኮሚቴ 2/3ኛ ድምፅ ግዴታዋን ያላሟላች እና የአመራር ብቃት የጎደላትን የብልግና ሴቶች ሊግ ማአከላዊ ኮሚቴ አባል ከአባልነት እስከ ጉባኤ አግዶ ያቆያል፡፡

7.12 ማአከላዊ ኮሚቴው ተግባርና ሀላፊነቱን በከፊል ለሊጉ ስራ አሰፈፃሚ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

# አንቀፅ 19

## የሴቶች ሊግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

1. የሊጉ ስራ አሰፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለማአከላዊ ኮሚቴ ሆኖ ከማአከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል በሚስጥር ድምፅ ይመረጣል፡፡
2. የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ በፕሬዝዳንቷ ይመራል፡፡
3. ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባውን በሶስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል ፡፡
4. አሰቸኳይ ስብሰባ በፕሬዘዳንቷ ወይም ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት 1/3ኛው ከጠየቁ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል፡፡
5. የስራ አሰፈፃሚ ኮሚቴ ምላዕተ ጉባኤ ከአባላቱ ከ50 %+1 የተገኙበት ይሆናል፡፡
6. **የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተግባርና ሀላፊነት የሚከተሉት ናቸው፡፡**

   7.1 በጉባኤውና በማአከላዊ ኮሚቴው የሚወጡ ዕቅዶች አቅጣጫዎች ውሳኔዎችና መመሪያዎች መከበራቸውን እና በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፤ ያረጋግጣል፤ አመራር ይሰጣል ፡፡

   7.2 የጉባኤና ማአከላዊ ኮሚቴ ውሳኔዎች እና ህገ ደንቡን መሰረት በማድረግ የሊጉን መመሪያዎች ያወጣል፤ ተግባራዊ መሆናቸውንም ይከታተላል፡፡

   7.3 ለማአከላዊ ኮሚቴው የስራ ዕቅድ እና ሪፖርት ያቀርባል፡፡

   7.4 በየደረጃው የሚገኙ የሊጉ አመራር የስራ እንቅስቃሴ ይመራል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል

   7.5 ለሊጉ ፅ/ቤት የስራ መምሪያ ይሰጣል፡፡

   7.6 በሊጉ የአመራር መዋቅር የአመራር ምደባ ያካሂዳል የአፈፃፀም መምሪያ በማውጣት ይፈፅማል፡፡

   7.7 የማአከላዊ ኮሚቴ አጀንዳ ያዘጋጃል፡፡

   7.8 የሊጉ ፕሮግራም፣ አቅጣጫወችና ውሳኔዎች ለሊጉ አባላት እና ለመላው ሴቶች ተደራሽ እዲሆኑ ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፡፡

   7.9የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውንም ሆነ ሌሎች አባሎች በተለያዩ የሊጉ ስራ ላይ ይመድባል

   7.10 የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ይሰይማል ዝርዝር የስራ መመሪያ ይሰጣል፡፡

   7.11 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከተግባርና ሀላፊነቱ በከፊል ለሊጉ ፕሬዘዳንት ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 20

## የሊጉ ፕሬዘዳንት

1. የሊጉ ፕሬዝዳንት ተጠሪነቷ ለማአከላዊ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖሯታል፡፡

1.1 የማአከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች በሰባሳቢነት ትመራለች፡፡

1.2 የማአከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስራዎችን ታስተባብራለች፡፡

1.3 የማአከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ታስፈፅማለች፡፡

1.4 የሴቶች ሊግን በመወከል ከተለያዩ አካላት ጋር ግንኙነት ታደርጋለች፤ ስምምነቶችን ትፈራረማለች፡፡

1.5 የስራ ሪፖርቱን ለስራ አስፈፃሚው ታቀርባለች፣ ለስራ አስፈፃሚ ስብሰባ አጀንዳ ታዘጋጃለች፡፡

1.6 የማአከላዊ ኮሚቴና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጧትን ሌሎች ተግባራት ታከናውናለች፡፡

## አንቀፅ 21

## የሊጉ ምክትል ፕሬዘዳንቶች

1. ሊጉ ምክትል ፕሬዝዳንቶች ይኖሩታል፡፡
2. ምክትል ፕሬዝዳንቶቹ ተጠሪነታቸው ለፕሬዘዳቷና ለማዕከላዊ ኮሚቴው ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡

   2.1 ፕሬዘዳንቷ በማትኖርበት ጊዜ የተወከለችው ምክትል ፕሬዘዳንት ተክታ ትሰራለች፡፡

   2.2 በማዕከላዊ ኮሚቴ፣ በስራ አስፈፃሚና በፕሬዘዳንቷ በሚሰጧቸውን የስራ ስምሪት መሰረት ስራቸውን ያከናውናሉ፡፡

## አንቀፅ 22

## የብልፅግና ሴቶች ሊግ ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን

1. የቁጥጥር ኢንስፔክሽን ኮሚሽን በሊጉ ጉባኤ በሚመረጡ አባላት ይዋቀራል ፡፡ ቁጥሩ በጉባኤ ይወሰናል፡፡
2. ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለሴቶች ሊግ ጉባኤ ነው፡፡

3. ኮሚሽኑ በየደረጃው በሚገኙ የሊጉ አደረጃጀት ፅ/ቤቶች ያደራጃል፤ የራሱን መዋቅር ይዘረጋል::

4. ኮሚሽኑ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት ይኖሩታል::

4.1. ኮሚሽኑ የሊጉን መተዳደሪያ ደንብና መመምሪያዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል::

4.2. የጉባኤ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ይከታተላል::

4.3. የሊጉ አባላት የሊጉን ፕሮግራም፤ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች መመሪያዎች ማክበራቸውን ለጠበቀ ዲስፕሊን ተገዥ መሆናቸውን ይከታተላል::

4.4. የሊጉ አባላትና አካላት መብቶችና ጥቅሞች መከበራቸውን ይከታተላል::

4.5. በአባላት የሚቀርቡ አቤቱታዎች ይቀበላል፤ ይመረምራል፤ የእርምት የውሳኔ ሀሳቡን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል::

4.6. ኮሚሽኑ ባሳለፈው ውሳኔ ላይ ከሴቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጋር የሀሳብ አንድነት ከተያዘበት ውሳኔው ተግባራዊ ይሆናል:: ልዩነት ከተከሰተ ልዩነቱ ወደ ሴቶች ሊግ ማአከላዊ ኮሚቴ ይተላለፋል:: ማአከላዊ ኮሚቴው የሚያሳልፈው ውሳኔ እስከ ጉባኤ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናል::

4.7. የሴቶች ሊግ ንብረትና ገንዘብ በትክክል መያዙንና በተቀመጠለት የአሰራር ስርዓት መሰረት ጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል:: የሊጉ የአባላት መዋጮ በወቅቱና በትክክል መሰብሰቡን ይቆጣጠራል ::

4.8. ጥፋት በሚፈፅሙ አባሎቹ ላይ የዲስፕሊን እርምጃ መውሰድ ይችላል:: አባሉን ማገድ ወይም ከስልጣኑ ማውረድ የሚችለው በአባላቱ 2/3ኛ ድምጽ ይሆናል::

4.9. ስለስራው ለሴቶች ሊግ ጉባኤ ሪፖርት ያቀርባል::

4.10. ኮሚሽኑ ከመካከሉ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሀፊ መርጦ ለጉባኤው ያስታውቃል፣

4.11. ኮሚሽኑ ይህን የመተዳሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ የራሱን አሰራርና መመሪያዎች ያወጣል::

4.12. ኮሚሽኑ በየሶስት ወሩ መደበኛ ስብሰባውን ያካሂዳል::

4.13. ኮሚሽኑ የራሱን አመታዊ እቅድ ያዘጋጀል ተግባራቱን ይመራል::

## አንቀፅ 23

### የብልፅግና ሴቶች ሊግ ጽ/ቤት

1. ጽህፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለሴቶች ሊግ ፕሬዘዳንት ነው፡፡
2. ጽህፈት ቤቱ ሀላፊ እና ምክትል ሀላፊዎች ይኖሩታል፣ አመራሮችም በስራ አስፈፃሚ ይመደባሉ፡፡
3. ጽህፈት ቤቱ በየወቅቱ ዕቅድና ሪፖርተ አዘጋጅቶ ለፕሬዘዳንቷ ያቀርባል፡፡
4. የጽህፈት ቤቱ አመራር ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡
5. ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

5.1 ጽህፈት ቤቱ በሴቶች ሊግ ውስጥ የሚካሄደውን ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ስራዎች፣ የፋይናንስና አስተዳደር ስራ በሃላፊነት ያከናውናል፡፡ የብልፅግና ሴቶች ሊግ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ሥራዎች ማዕከል ሆኖ ይንቀሳቀሳል፡፡

5.2 የሴቶች ሊግ ማአከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ውሳኔዎች መሰረት በማድረግ የሴቶች ሊግ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ስራ ያቅዳል፤ ያስፈፅማል፡፡ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤ ይቆጣጠራል፡፡

5.3 የሴቶችን ሊግ ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ እቅዶቹንና የስራ አፈፃፀም ለሴቶች ያስተዋውቃል፤

5.4 በሴቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚ በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት የሴቶች ሊግ ፋይናንስና ንብረት  እንዲሁም የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል፡፡

5.5 የሴቶች ሊግ ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውንና ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

5.6 ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከፕሬዘዳንቷ በሚሰጠው መመሪያና ከብልፅግና - ርቲ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ይበለጽግና ሴቶች ሊግን ወክሎ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡

5.7 የሴቶች ሊግን በመወከል  ውል ይዋዋላል ይከሳል ይከሰሳል፡፡

5.8 ስለ ስራው አፈፃፀም ለሴቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለፕሬዘዳንቷ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

5.9 ጽ/ቤቱ ከተግባርና ሀላፊነቱ ለክልል ሊግ ፅ/ቤቶች ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

5.10 ስለ አሰራሩ ዝርዝር መመሪያ በሊጉ ስራ አስፈጻሚ ይወጣል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የሊጉ የክልል አደረጃጀት

## አንቀፅ 24

## የሊጉ አደረጃጀትና አወቃቀር

1. ለሊጉ ዋና ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ የክልል የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ ፅ/ቤቶች የክልል ስያሜ በመያዝ እደሚከተለው ተቋቁመዋል
   ሀ. የኦሮሚያ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽህፈት ቤት
   ለ. የአማራ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽህፈት ቤት
   ሐ. የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽህፈት ቤት
   መ. የሶማሌ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽህፈት ቤት
   ሠ. የቤንሻንጉል ጉምዝ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽህፈት ቤት
   ረ. የትግራይ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽህፈት ቤት
   ሰ. የአፋር ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽህፈት ቤት
   ሸ. የጋምቤላ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽህፈት ቤት
   ቀ. የሀረሪ ብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽህፈት ቤት
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ(1) የተደነገገው እደተጠበቀ ሆኖ ለሊጉ ዋና ፅ/ቤት ተጠሪ የሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር የሊግ ፅ/ቤቶች ይቋቋማሉ፤ እንዲሁም በየደረጃው የክፍለ ከተማ እና የወረዳ አደረጃጀቶች ይኖራቸዋል፡፡
3. ለክልል የሊጉ ፅ/ቤቶች ተጠሪ የሆኑ የዞኖች ወረዳዎች /ልዩ ወረዳዎች ፤ የከተሞች እና የቀበሌዎች ፅ/ቤቶች ይኖሩታል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እስከ (3) የተቋቋሙት ፅ/ቤቶች በየደረጃው የሊጉ ኮንፍራንንስ፤ አሰተባባሪ ኮሚቴዎች፤ ፅ/ቤቶችና፤ የቁጥጥር ኢንስፔክሽን ኮሚቴዎች ይኖሯቸዋል ፡፡

## አንቀፅ 25

## የክልል የሊጉ ኮንፍራንስ የአሰራር ስርዓት

1. የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፣ የከተማ አስተዳደርና የቀበሌ የሊጉ ኮንፍራንሶች በየደረጃው የሊጉ አባላት የፖለቲካ ግንባታ መድረክ ሆነው ያገለግላሉ ፡፡

2. የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፣ የከተማ አስተዳደር እና የቀበሌ የሊጉ ኮንፍራንሶች ውክልና ስብጥር በአባላት ብዛት ሆኖ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች ተሳትፎ እንዲያረጋግጥ ተደርጎ ይወሰናል ፡፡
3. የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፣ የከተማ አስተዳደር እና የቀበሌ የሊጉ ኮንፍራንሶች በየደረጃው በሚገኘው የሊጉ አስተባባሪዎች ጠሪነት የሚሰበሰብ ሆኖ የክልል፣ የዞን፤ የወረዳ የከተማ ኮንፍራንሶች በዓመት አንድ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን የቀበሌ/መሰረታዊ ድርጅቶች በየሶስት ወሩ ኮንፈረሳቸውን ያካሂዳሉ፡፡
4. የክልል የቁጥጥር እና ኢንስፔክሽን ኮሚቴዎች አጠቃላይ የስራ ሂደት እና ፖሊቲካዊ ሁኔታ በክልል የሊግ ኮንፍራንሶች ላይ ይገመገማል፡፡

### አንቀፅ 26

### የሊጉ ኮንፈረንስ ተግባርና ሀላፊነት

1. በየደረጃው የሊጉ ፕሮግራም እና መተዳደሪያ ደንብ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡
2. የሊጉ አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎች፣ ዕቅዶች በትክክል መተግበራቸውን ያረጋግጣል፡፡
3. የአባላቱ የፖለቲካ ብቃት እዲዳብር ያደርጋል፡፡
4. በሊጉ የጉባኤ እና የኮንፈረስ ተሳትፎና ውክልና መመሪያ መሰረት ለሊጉ ጉባኤ እና በየደረጃው ለሚካሄዱ ኮንፈረሶች አባላትን ይወክላሉ ፡፡
5. በየደረጃው ከሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴ እና ከቁጥጥር ኢንስፔክሽን ኮሚቴ የሚቀርብለትን ዕቅድ እና የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ያዳምጣል፤ ይገመግማል፤ ያፀድቃል ፡፡

### አንቀፅ 27

### የሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴ

1. የክልል ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሊጉ የስራ አስፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. የዞን፣ ወረዳ ከተማና ቀበሌ ሊግ ኮሚቴ አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለሚገኙት የሊግ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ተጠሪ ይሆናሉ፡፡
3. የክልል ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ በየወሩ አንድ ጊዜ፤ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ አስተዳደር እና የክፍለ ከተማ በወር ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
4. በየደረጃው የሚገኙ አስተባባሪ ኮሚቴዎች የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

4.1በቀጠናቸው የሊጉን የፖሊቲካና የድርጅት ስራዎች በበላይነት ያስተባብራሉ፡፡

4.2ከሊጉ የበላይ አካል የሚተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በተግባር ያውላሉ፡፡

4.3በየደረጃው የሚገኙት የሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ምደባ እና የውሳኔ ሀሳብ ቀጥሎ ላለው የሊግ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፤ ሲፀድቅ ያሰማራሉ፡፡

4.4ስለ ስራው ክንውን ቀጥሎ ላለው የሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## አንቀጽ 28

## በየደረጃው ያሉ የብልጽግና - ርቲ የሴቶች ሊግ ጽሕፈት ቤቶች

1. የሊጉ ጽ/ቤቶች በየደረጃው የሊጉ የፖለቲካ፣ የድርጀትና የህዝብ ግንኙነት ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ፡፡
2. የጽ/ቤቶቹ ተጠሪነታቸው አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለሚገኙት የሊጉ ጽ/ቤቶች ይሆናል፡፡
3. ጽ/ቤቶች በስራ አስፈጻሚ ወይም በየደረጃው ባሉ የሊግ አስተባባሪ ኮሚቴዎች የሚሰየሙ ሀላፊና ምክትል ሀላፊዎች ሊኖራቸው ይችላል፡፡
4. የሊጉ ጽ/ቤቶች የሚከተሉት ተግባራት እና ሀላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡

4.1የሊጉን ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ስራ ያቅዳል፤ ያስፈፅማል፤ ይደግፋል አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

4.2የሴቶችን ሊግ ፕሮግራም አቅጣጫዎች፣ እቅዶቹንና የስራ አፈፃፀም ለሴቶች ያስተዋውቃል፡፡

4.3የሴቶች ሊግ ፋይናንስና ንብረት እንዳሁም የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል፡፡

4.4ከሊጉ ዋና ጽ/ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ሴቶች ሊግን ወክሎ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤.

4.5ጽ/ቤቶች በየወቅቱ ዕቅድና ሪፖርት አዘጋጅተው በየደረጃው ላሉት ሊግ ጽ/ቤቶች ሪፖርት ያቀርባሉ ስለ ስራው አፈፃፀም ለአስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

4.6በየደረጃው ባሉት የሊጉ አደረጃጀቶች የሚሠጡ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናሉ፡፡

## አንቀፅ 29

## በየደረጃው ያለ የሊጉ የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ

1 ክልላዊ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሊጉ ቁጥጥርና ዚንስፔክሽን ኮሚሽ ሆኖ ከክልል በታች ያለው ኮሚቴ ተጠሪነቱ አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለሚገኙት የሊጉ የቁጥጥር ኢንስፔክሽን ኮሚቴዎች ይሆናል ፡፡

2 ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት ይኖሩታል፤

2.1 የሊጉ አባላት የሊጉን ፕሮግራም፤ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች መመሪያዎች መከበራቸውን ለዲስፕሊን ተገዥ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡

2.2 የሊጉ ኮንፈረስ ውሳኔውች አቅጣጫወች በአግባቡ መፈፀማቸውን ይከታተላል ፡፡

2.3 የሊጉ አባላትና አካላት መብቶችና ጥቅሞች መከበራቸውን ይከታተላል፡፡

2.4 በአባላት የሚቀርቡ አቤቱታዎች ይቀበላል፤ ይመረምራል፡፡

2.5 የሴቶች ሊግ ንብረትና ገንዘብ  በትክክል መያዙንና በተቀመጠለት የአሰራር ስርዓት መሰረት ጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡

2.6 የሊጉ የአባላት መዋጮ በወቅቱና በትክክል መሰብሰቡን ይቆጣጠራል፡፡

2.7 ስለስራው አፈፃፀም ለሊጉ ኮንፈረስ እና ቀጥሎ ላለው የቁጥጥር ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

2.8 ኮሚቴው ከመካከሉ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሀፊ መርጦ ለኮንፈረሱ ያስታውቃል፡፡

## አንቀፅ 30

## ከብልፅግና ፓርቲ ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት

1. የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ የፓርቲው አንድ ክንፍ ነው፡፡ በመሆኑም ከብልፅግና ፓርቲ ጋር ያለው ግንኙነት የፓርቲውን አመራር በመቀበል ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ ብልፅግና ፓርቲን በመወከልም በሴቶቹ ውስጥ የሚሰራ ስራ ያከናውናል፡፡
2. የብልፅግና - ርቲ ሴቶች ሊግ እራሱን የቻለ የሴት አደረጃጀት ሆኖ ከብልፅግና - ርቲ መዋቅር ጋር በየደረጃው ተሳስሮ የሚዋቀር ሲሆን - ርቲው የሚመራባቸውን መንገዶች እና መርሆዎች በዕምነት ተቀብሎ ለተግባራዊነታቸው በፅናት ይታገላል፡፡
3. የሴቶች ሊግ በየደረጃው ከብልፅግና - ርቲ ጋር በቅርበት ይሰራል፤ የድርጅቱን ውሳኔዎች ያከብራል፤ ከሊጉ ሁኔታ ጋር በማጣጣም በስራ ላይ ያውላል፡፡
4. የብልጽግና ሴቶች ሊግ የብልጽግና ፓርቲ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በየደረጃው ባሉ የፓርቲው የአመራር እርከኖች የኮሚቴ አባል በመሆን እንዲሁም በፓርቲው ጉባኤ ላይ ፓርቲው በሚፈቅደው የአባላት ቁጥር በጉባኤተኛ አባልነት ይሳተፋል፡፡
5. ሴቶች በፓርቲ ውስጥ በወጡ ደንቦች መመሪያዎች ተግባራዊነታቸው እንዲጎለብት አጠናክሮ የሚሰራ ሲሆን የሴቶች በየደረጃው የውሳኔ ተሳትፏቸው ከፍ እንዲል፣ በምርጫ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ይበልጥ እንዲሳተፉ ርብርብ ያደርጋል፡፡

## አንቀፅ 31

### የብልፅግና ሴቶች ሊግ ከሌሎች የሴት አደረጃጀቶች ጋር ስለሚያደርጉት ግንኙነት

1. በአገሪቱ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ ሕገ መንግስቱን አክብሮ ከሚሰሩ ማህበራት ጋር በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች እና በሴቶች አጀንዳዎች ላይ አብሮ መስራት ይችላል፡፡

2. በሃገራችን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የጎላ አስተዋፅኦ ለማድረግ ዝግጁ የሆኑ የመልካም አስተዳደር ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ከሚያደርጉ የተለያዩ ማህበራት ጋር በፌደሬሽን እና ኮንፌዴሬሽን ተደራጅቶ ሊሰራ ይችላል፡፡
3. በአገራዊ እና አለም አቀፋዊ ግንኙነቶች በተመለከተ ማህበራቱ ዲሞክራሲያዊ እስከ ሆኑ ድረስ አብሮ መስራት ይችላል፡፡
4. በሴቶች ዙሪያ ከሚሰሩ ማንኛውም መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማቶች ጋር ስለ ሴቶች ሁለተናዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በጋራ ይሰራል፡፡

## ምዕራፍ 5

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ 32

### የስልጣን ዘመን

1. የሊጉ ፕሬዘዳንት እና ምክትል ፕሬዘዳንቶች የሀላፊነት ዘመን ጣሪያ አስር አመት ይሆናል፡፡
2. የሊጉ አመራር የዕድሜ ጣሪያ ስልሳ አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

### እንቀፅ 33

### የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በእናት በ- ርቲው መዋሀድ እና የ4ኛው የኢህአዳዴግ ሴቶች ሊግ ጉባኤ በሰጠው አቅጣጫ መሰርት የእናት ፓርቲውን የለውጥ አቅጣጫ በመከተል የኢሀአዲግ ሴቶች ሊግ አባል ሊጎች የአጋር ፓርቲ ሊጎችን ጨምሮ ወደ አንድ ሀገራዊ የብልፅግና ሴቶች ሊግ ውህደት በዚህ ደንብ ተከናውኗል ፡፡
2. የኢህአዴግ አጋር ፓርቲዎች የሴቶች ሊጎች የነበራቸው የተናጥል መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ወደ ብልፅግና ሴቶች ሊግ ተላልፏል፡፡
3. የብልፅግና ሴቶች ሊግ ጉባኤ እስኪካሄድ ድረስ የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ ምክር ቤትና ስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሁም የቁጥጥር እና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን የሊጉ አመራር ሆነው ይቀጥላሉ፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጋር ሴቶች ሊግ በማእከላዊ ኮሚቴ እና በስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ የሚሳተፉ አባላት ብዛት የሊጉ ስራ አሰፈፃሚ ከአጋጋ - ርቲ ሴቶች ሊግ አመራሮች ጋር ተወያይቶ በወሰነው ውሳኔ መሰረት ሊቀመንበርና

ምክትል ሊቀመንበር በስራ አስፈጻሚ እንዲሁም ሁሉም ስራ አስፈጻሚዎች በምክር ቤቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ብልጽግና ሴቶች ሊግን የመሠረቱ የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ አባል ሊጎችና አጋር ሊጎች የክልል፣ የዞንና የወረዳ ስራ አስፈጻሚዎች የነበሩት የብልጽግና ሴቶች ሊግ የክልል፣ የዞንና የወረዳ የሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ይሆናሉ፡፡
6. የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ አባላት እና የኢህአዴግ አጋር - ርቲዎች ሴቶች ሊግ አባላት ያለ ቅድመ ሁኔታ የብልፅግና ሴቶች ሊግ አባል ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

## አንቀፅ 34

## የብልፅግና ሴቶች ሊግ የፋይናንስ ምንጭ

የብልፅግና ሴቶች ሊግ የፋይናንስ ምንጭ ከሴቶች ሊግ አባል መዋጮ እንዲሁም በብልፅግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ከኢትዮጵያውያን ደጋፊዎችና ወዳጆች በሚደረግ ድጋፍ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 35

### መመሪያ የማውጣት ስልጣን፡-

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ለተለያዩ አካላት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የብልፅግና ሴቶች ሊግ ማአከላዊ ኮሚቴ ይህን መተዳደሪያ ደንብ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

## አንቀፅ 36

## መተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል፣ መቀየርና መሻር፤

1. ይህን መተዳደሪያ ደንብ ሊያሻሽል፣ ሊቀይርና ሊሽር የሚችለው የብልፅግና ሴቶች ሊግ ጉባኤ ብቻ ነው፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እደተጠበቀ ሆኖ የመተዳደሪያ ደንቡ የማሻሻያ ሀሳብ ሊቀርብ የሚችለው፡

   ሀ. በፕሬዘዳንቷ

   ለ. በማአከላዊ ኮሚቴው 1/3 ድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ወይም

   ሐ. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አብላጫ ድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ወይም

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (2) መሰረት የቀረበ የማሻሻያ ሀሳብ ለሊጉ ጉባኤ መቅረብ የሚችለው በማአከላዊ ኮሚቴው በአብላጫ ድምጽ ድጋፍ ካገኘ ነው::
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) መሰርት በማእከላዊ ኮሚቴ በቀረበው የማሻሻያ ሀሳብ ላይ የሊጉ ጉባኤ በአብላጫ ድምጽ ከወሰነ መተዳደሪያ ደንቡ ይሻሻላል::

## አንቀፅ 37

## መተዳደሪያ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በጉባኤ ከፀደቀበት ከ-----------------ቀን -------------- ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::